PRESS RELEASE

ጋዜጣዊ መግለጫ ቁጥር 20/199

# የዓለም ዓቀፍ የገንዘብ ተቋም /አይ ኤም ኤፍ/ የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ ኢትዮጵያ የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከል ለምታደርገው ዘመቻ የሚውል የ411 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር አስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ አፀደቀ

**አስቸኳይ መግለጫ**

**ሚያዚያ 22, 2012**

- የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ባስከተለው ጉዳት የተነሳ ኢትዮጵያ ጉልህ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ያጋጠማት ሲሆን ይህንን ለመቋቋም የሚያስችል አጣዳፊ የውጭ ክፍያ ሚዛን ድጋፍ አስፈልጓታል፡፡
- ችግሩም አፋጣኝ ምላሽ የሚያስፈልገው በመሆኑ የአለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም /አይ ኤም ኤፍ/ ለኢትዮጵያ ከተቋሙ የአስቸኳይ ጊዜ ፋይናንስ አቅርቦት ማዕቀፍ (Rapid Financing Instrument) የ411 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ድጋፍ እንድታገኝ ወስኗል፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያ ከዓለም ዓቀፍ ገንዘብ ድርጅት የአደጋ ጊዜ መከላከል እና የዕፎይታ ትረስት ማዕቀፍ (Catastrophe Containment and Relief Trust) የዕዳ ክፍያ ዕፎይታ ተጠቃሚ እንደምትሆን ተገልጿል፡፡
- የአገሪቱ ባለስልጣኖች የኮቪድ 19 ወረርሽኝ የሚያስከትለውን አደጋ ለመከላከል የጤና አገልግሎቶችን የማጠናከር፣ እንዲሁም የቫይረሱን ስርጭት ለመገደብ የሚያስችል የአስቸኳይ ጊዜ በሥራ ላይ የማዋልና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን ለመደገፍ የሚያስችሉ አፋጣኝና ወሳኝ እርምጃዎችን መውሰዳቸው ታውቋል፡፡

**ዋሽንግተን ደ..ሲ. ሚያዝያ 22/ 2012**፡ የዓለም ዓቀፍ የገንዘብ ተቋም /አይ ኤም ኤፍ/ የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ በዛሬው ዕለት የአስቸኳይ ጊዜ ፋይናንስ አቅርቦት ማዕቀፉ የ300.7 ሚሊዮን ኤስዲአር (የ411 ሚሊዮን ዶላር የአገሪቱን ኮታ 100 በመቶ) ኢትዮጵያ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ለመከላከል የሚያስፈልጋትን የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ለመደገፍ የሚስችላትን ድጋፍ አጽድቋል፡፡ የሥራ አስፈጻሚ ቦርዱ አገሪቱ የዘረጋችውን የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ለመተግበር ከታህሳስ 2012 ጀምሮ ከድርጅቱ የብድር ማዕቀፎች (Extended Credit Facility (ECF) እና (Extended Financing Facility (EFF) ) በወሰደቻቸው ብድሮች ላይ የብድር

አቅርቦት ፍሰት ማሻሻያ እንዲደረግ ወስኗል፡፡ ውሳኔው ኢትዮጵያ ከአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ ማዕቀፍ ተጨማሪ እርዳታ እንድታገኝ የሚያስችልም ነው፡፡

ከዚህም በላይ ኢትዮጵያ የተቋሙ ቦርድ ለድንገተኛ አደጋ ተጋላጭና ድሃ አገሮች በሚያዝያ 5 2012 ከዘረጋው የአስቸኳይ ጊዜ ፋይናንስ አቅርቦት እና የዕፎይታ ትረስት የእዳ ክፍያ እፎይታ ስርዓት ተጠቃሚ እንደምትሆን ታውቋል፡፡ በመሆኑም ቦርዱ በዛሬው ዕለት ኢትዮጵያ ከተቋም የአደጋ ጊዜ መከላከል እና የዕፎይታ ትረስት ማዕቀፍ እስከ ጥቅምት 3/ 2013 ዓ.ም መክፈል ያለባትን የ12 ሚሊዮን ዶላር የእዳ ክፍያ እፎይታ እንዲደረግላት ያቀረበቸውን ጥያቄ በአዎንታ ተቀብሏል፡፡ የእዳ ክፍያ እፎይታው የአደጋ ጊዜ መከላከል እና የዕፎይታ ትረስት ማዕቀፉ በቂ ፋይናንስ የሚኖረው ከሆነ እስከ ሚያዝያ 5/ 2014 ሊዘልቅ አንደሚችል ታውቋል፡፡

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ከፍተኛ የጤና ስጋት ከመፍጠሩም በላይ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ከባድ ጫና አሳድሯል፡፡ ወረርሽኙ በአጭር ጊዜ ካልተገታ በጤና አግልግሎቱ ላይ ከፍተኛ ጫና ከመፍጠሩም በላይ መውጫ የሌለው ማህበራዊ ቀውስ እንደሚያስከትል ይታመናል፡፡ በኢኮኖሚው ዘርፍም የውጭ ንግድ ሸቀጦች ፍላጎት መቀነስ፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ በሚወሰዱ የእንቅስቃሴ መገደብ እርምጃዎች የተነሳ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ በማጋጠሙ የውጭ የክፍያ ሚዛንና የበጀት ጉድለት መዛባት መከሰቱ ግልጽ ነው፡፡

የአገሪቱ ባለስልጣኖች የኮቪድ 19 ወረርሽኝ የሚያስከትለውን አደጋ ለመከላከል ከውጭ አገር የሚገቡ መንገደኞች በግዳጅ ለ14 ቀናት በለይቶ ማቆያ እንዲስተናገዱ የማድረግ፣ እንዲሁም የምርመራና ተገሎ የማቆየት አሰራርን አቅም የማጎልበት ተግባራትን አከናውነዋል፡፡ ከዚህም በላይ የወረርሽኙን መስፋፋት ለመቋቋምና የቫይረሱን ስርጭት ለመገደብ የሚያስችል እንቅስቃሴን ለመወሰን፣ ህዝባዊ ስብሰባዎችን ለማገድ፣ እንዲሁም ማህበራዊ ርቀትን መጠበቅን የሚያስገድድ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሥራ ላይ እንዲውል አድርገዋል፡፡ የጤና አገልግሎትን ለማጎልበትና የምግብ ዋስትና ተግዳሮትን ለመቋቋም የተደረገው ጥረት የሚያስመሰግን ሲሆን ድርጊቱም የቫይረሱን ስርጭት ለመቀነስና ተጋላጭና ድሀ የህብረተሰቡን ክፍል ለመደገፍ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

ተቋሙ የኢትዮጵያን ሁኔታ በቅርበት መከታተሉን የሚቀጥልና እንደ አስፈላጊነቱም የፖሊሲ ምክርና የገንዘብ ድጋፍ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በሥራ አስፈጻሚው ቦርድ ውይይት መድረክ ማጠናቀቂያ የተቋሙ ምክትል ማኔጅንግ ዳይሬክተርና የውይይቱ መድረክ መሪ ሚ/ር ታኦ ጃንግ (Mr. Tao Zhang) የሚከተለውን መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

“ኢትዮጵያ ለውጭ አደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስና በግሉ ዘርፍ ወደሚመራ ኢኮኖሚ ስርዓት ለመሸጋገር የምታደርገው ጥረት በዓለም ዓቀፍ የገንዘብ ድርጅት ድጋፍ ታግዞ ከፍተኛ እድገት የታየበት ነው፡፡ የአገሪቱ ባለሥልጣኖች ለዘረጉት የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ተግባራዊነት ቁርጠኛ መሆናቸው በተግባር የተረጋገጠ ነው፡፡ ሆኖም የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ያስከተለው ተጽዕኖ አፋጣኝ የውጭ ምንዛሬና የመንግሥት ፋይናንስ አቅርቦት ፍላጎትን አስከትሏል፡፡ በዚህ ረገድ የአገሪቱ የመንግሥት ባለሥልጣኖች የወረርሽኙን ስርጭት ለመገደብ እንዲሁም በዓለም ዓቀፍ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ የተነሳ የሚከሰተውን የኢኮኖሚ ጫና ለመቋቋምና የጤና አገልግሎት እርምጃዎችን ለመወሰድ ቁርጠኝነት አሳይተዋል”፡፡

“በዚህ ወቅት ጊዜያዊ የበጀት ጉድለት መኖር የሚነቀፍ አይሆንም፡፡ ለጤና አጠባበቅ የሚውለውን በጀት እና የአደጋ ጊዜ እርዳታን ማሳደግ ግምባር ቀደም ትኩረት ማግኘት ያለበት መሆኑ ይታመናል፡፡ ባለሥልጣኖቹ ከአደጋ ጊዜ እርዳታ ጋር ተያይዞ የሚከናወኑ ወጪዎች አፈጻጸም ግልጽነት እንዲኖራቸውና ወረርሽኙ ከተወገደ በኋላም አስፈላጊውን ኦዲት ለማድረግ ቁርጠኛ ናቸው፡፡ ወረርሽኙ ያስከተለው ቀውስ ከተወገደ በኋላም የዕዳ አስተዳደርንና የመንግሥት ገቢ አሰባሰብን የማጎልበት ተግባራት ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል”፡፡

“የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የንግድ ባንኮችን ፋይናንስ የማቅረብ አቅምና ዘላቂነት ለመደገፍ የወሰዳቸው እርምጃዎች አበረታች ናቸው፡፡ ወረርሽኙ ከተወገደ በኋላም የዋጋ ንረትን በነጠላ ቁጥር ለመገደብ የሚያስችለውን ጠበቅ ያለ የገንዘብ ፖሊሲ መተግበር ተገቢ ነው፡፡ የውጭ ምንዛሬ ተመኑ የውጭ ክፍያ ሚዛን የማረጋጋት ሚናውን ለመጫወት እንዲችል የብር የውጭ ምንዛሬ የመግዛት አቅምን መዛባት ለማስተካከል ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ግዴታ ነው”፡፡

“የዓለም ዓቀፍ የገንዘብ ተቋም ለኢትየጵያ ከአስቸኳይ ጊዜ የፋይናንስ ድጋፍና (Rapid Financing Instrument) ከአደጋ ጊዜ መከላከል እና የዕፎይታ ትረስት ማዕቀፍ (Catastrophe Containment and Relief Trust ) ያደረገው የፋናንስ ድጋፍና የእዳ ስረዛ የአገሪቱን የውጭ ክፍያ ሚዛን ተግዳሮት ለማቃለልና

ወረርሽኙን ለመከላከል ለሚውል የፋይናንስ አቅም እንደሚፈጥሩ ይታመናል፡፡ በቡድን 20 የእዳ ስረዛ መድረክ በመሳተፍም ወረርሽኙን ለመከላከል የሚያስችል ተጫማሪ የፋይናንስ አቅም መገንባት እንደሚቻል ይታመናል"፡፡

***ተጨማሪ መረጃ***

የዓለም ዓቀፍ የገንዘብ ድርጅት የብድር መረጃ ማጣቀሻ (የዓለም ዓቀፍ የገንዘብ ድርጅት የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ የድንገተኛ አደጋ ፋይናንስ ጥያቄን አጸደቀ)

https://www.imf.org/en/Topics/imf-and-covid19/COVID-Lending-Tracke

የዓለም ዓቀፍ የገንዘብ ድርጅት ሥራ አስፈጻሚ ቦርድ አጀንዳ

https://www.imf.org/external/NP/SEC/bc/eng/index.aspx